*ከደርግ ቀይሽብር ጀምሮ ያለው ትውልድ ፈሪ ነው ተብሎ ይከሰሳል፤ ለምን? ይህ አባባል አርበኛ ፋኖችን አያካትትም*

Tatek Menji, [25/ 12/2024

*ሀ) ትውልዱን ፈሪ ካሰኘው ማሳያ ነጥቦች ጥቂቶቹ ፡-*

- *አውደ የአማራ ሕዝብ በብሄር ማንነቱ–ሲጨፈጨፍ፣ ከቀዬው ሲፈናቀል፣ሃብት ንብረቱን ሲወድም –በሌሎች የኢትዮጵያ ምድር የሚኖር –የአፋር፣ የደቡብ፣ የምሥራቅ ፣ የቤኒሻንጎል፣ የሲዳማ ወዘተርፈ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዝምታ፣ እጅና እግር አጣምሮ መቀመጥ ምክንያት ፍርሃት አይደለምን?*

*ያ ባይሆን ኖሮ ጠመንጃ አንስቶ ከወገኑ ከአማራ ሕዝብ ጎን ይሰለፍ ነበር ። ጠመንጃ የማንሳት ድፍረት/ወኔ ካጣ ትንሽ መስዋዕትነት የሚያስከፍለው – በየአካባቢያቸው ተከታታይ ሰልፍ በመጥራት የአማራን ዘር ለማጥፋት ፣ሃብትና ንብረቱን ለመደምሰስ/ለማውደም የታወጀው ጦርነት ይቁም ማለት፤ መቃወም፣ ማመጽ ወዘተርፈ ይገባው ነበር ።*

*ለምንድ ነው አያትና ቅም አያቶቻችን –ከግብጾች፣ ከቱርኮች፣ከደርቡሾች፣ ከመሃመድ ግራኝ ወዘተርፈ ወረራዎች ቢጋራ የተፋለሙት ? ለምንድ ነው አያቶቻችንና አባቶቻችን ከጣሊያን ወራሪ ሠራዊት ቢጋራ የተፋለሙት? ሏዓላዊነታቸውን፣ ዳር ድንበራቸውን፣ አገራዊና ሕዝባዊ አንድነታቸውን ለማስከበር አልነበረምን? አይደለምን?*

*በአብይ አህመድ መሪነት እና በብርሃኑ ጁላ አዝማችነት በአማራ ወገኖቻችን ላይ የታወጀውን ጦርነት ዓላማና የሚያስከትለው መዘዝ ከባዕዳን ወራሪዎች ፍላጎትና ጥፋት የከፋ እንጂ የሚያንስ ነውን? ታዲያ እንደ ቀደምቶቻችን ቢጋራ ተነስተው ይህንን በአማራ ላይ የታወጀው ጦርነት፣ በአማራ ላይ የዘመተን የአሆዴድ ሠራዊት ያልተቃወሙት /የማይቃወሙት ? ይህኛው ከውስጥ በራሱ ገዢዮች የሚፈጸም ስለሆነ ነውን?*

በባንዳ ወያኔ የኢትዮ– ባንድራ ሽፋን –የኦሮምማ የበላይነት በማስፈን አስተምሮትና ቅኝት ተደራጅቶ የሚንቀሳቀስ ሠራዊት ስለሆነ –ለአብይ አህመድ ጽጥ ለጥ ብለው በማይገዙ በሁሉ የአስተዳደር ወሰኖች/ክልሎች በሚኖሩ ብሄር ብሄረሰቦች ሁሉ ላይ የሚዘምት፣የሚገልና የሚጨፈጭፍ ሠራዊት ነው ። ፍርሃት ካልሆነ የደቡብ ፣የአፋር ፣የምሠራቅ፣ የቤኒሻንጎል፣የሲዳማ ወዘተርፈ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሪዮች ይህንን አደጋ አያውቁትም፤ አልተረዱትም ማለት አይቻልም ።

- በአ/አበባ በኮሪደር ልማት ስም –ያለነዋሪዩ ፍቃድ ከቅም አያት፣ አያትና አባት በቤተሰብ ውርስ የተገኙ ቤቶች ፈርሷል፣ እርስቶች ተቀምቷል
- ያለፍቃዳቸው የብዙ ሺዮች መኖርያ ቤቶችና ንግድ ቤቶች ፈርሷል
- አ/አ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካም እምብርት ነው ። የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ጥንታዊና ዘመናዊ {የታሪክ፣ የትምህርት፣ የባህል፣ የቲያትር፣ የፊልም፣ የሃይማኖቶች፣ የሃገር መንግሥት ግንባታ ተቋማትና ቅርሶች} ወዘተርፈ እምብርት/መአከል ነው ። ከመቶ ሃያ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ ቤተሰብ ቢያንስ አንድ የቤተሰብ አባል በአ/አ ይኖራል ። በመሆኑም አ/አ ከመፍረስ ጋር ግንባር ቀደም ተጠቂና ተጎጂ የአ/አ ነዋሪዮች ይሁኑ እንጂ በሁሉ ጎኑ ሞላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠቅቷል ።
- በመጀመርያ የአ/አ ነዋሪዎች ፣በሁለተኛ ከአ/አ ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ፤ የአገራቸውን እርእስ ከተማ ሲፈርስ የሌላ አገር ከተማ ሲፈርስ ቁጭ ብለው የሚያዩ ይመስሉ ነበር/ይመስላሉ ። ያለ ሕዝቡን ፍቃድና አውንታ ብሄራዊ/የአገሩን ዋና ከተማ ሲፈርስ ፤ ቁጭ ብሎ የሚያይ ሕዝብ ያለበት አገር አለን ?
- አራስ እናት ከነህጻኗ ጋር፣ ህጻናት፣ ብላቴናዎች ፣አዛውንቶች፣በሽተኞች፣ አካለ ስንኩሎች ወዘተርፈ በተኙበት እላይ ላያቸው ቤቶቻቸውን ሚያፈርስ
- ያጡ ፣የነጡ ደሆች ላልሞት ባይ ተጋዳይ (for existence) የዳቦ መግዣ ለማግኘት በሚነግዱበት ሱቅ ውስጥ እያሉ እላያቸው ላይ ሱቃቸውን የሚያፈርስ

- አንዱን ብሄር በለሌላ ብሄር ላይ የሚያዘምት/የሚያስነሳ ፤ የአንድን ሃይማኖት ተከታዮች በሌላ ሃይማኖት ተከታዮች ላይ እንዲነሱ/ዘምቱ የሚቀሰቅስ፣ የአንድን ሕገ ሃይማኖት/ሲኖዶስ የሚከፋፍል
- በብሄር ማንነታቸው ብዙ ሺዮች ያስጨፈጨፈ፣ከቄያቸው ያፈናቀለ ፣ያስራበ ላሳርና ለመከራ የዳረገ
- የሚገዛውን ሕዝብ የሚንቅ ፣የሚያንቋሽሽ፣ ድሃና የድሃ ቤቶች በዓይኑ ማየት የማይፈልግ
- የሃይማኖት አባቶች ከነ ቤተሰባቸው የሚያስገድል ፤ የሰብአዊና የፖለቲካ መብቶች ተሟጋቾችን አሳፍኖ የሚሰውር፣ የሚያስር፣ሚገል፣የሚያሳርድ ወዘተርፈ
- የሚገዛውን ሕዝብ አባል/ላት አሳፍኖ ሃብት ንብረታቸውን የሚያዘርፍ፤ የሚገዛውን አገር ባንክ አዘርፎ ለብሄሩ

  ሽፍቶች መደራጃ የሚያውል
- የመኖር ተስፋ አሳጥቶ ራሱን የሚያጠፋ ዜጌ እንዲፈጠር ያደረገ
- የሥልጣን ዘመኑ ለማራዘም ጦርነትና እልቂት አስነስቶ የራሱን ብሄር አባል አሳርዶ ፣ የእገሌ ብሄር ነው ያረደው ብሎ ፕርፓጋንድ የሚያሰራ
- አገራዊና ሕዝባዊ አንድነትን ለማፈራረስ የሚጥር፤ ይህንን ለማድረግ የሚጥር መሆኑን በይፋ የሚናገር
- የአውደ ሕዝቡን ሕይወት የምድር ሲዖል ባደረገ ፍጹም አምባገነን(despotic/tyrant)ገዢና ሥርዓቱ ላይ –አለመነሳት፣አለመቃወም፣ አለማመጽ ወዘተርፈ ፍርሃት ብቻ ሳይሆን በድንነት አይደለምን?

  በደመነፍስ ወይም በዳበሳ የሚኖሩ እንስሳት እንኳን ቄያቸውን/ድንበራቸውን (territory) በሚደፍር ማንኛውም ፍጥረት/ግኝት ላይ ይነሳሉ/ያምጻሉ፤ ድንበራቸውን ያስከብራሉ ። የአሁኑ ትውልድ፣ የአሁኑ የማኅበረሰባችን የፍርሃት ደረጃ ከደመነፍስ እንስሳት ባህሪ ዝቅ ያለ አይመስልምን?

- የኬኒያውያን፣ የሴኔጋላውያን፣ የናይጀሪያውያን ወዘተረፈ አመጾች የተደረጉትና የታዩት ኣ/አበባን ማፍረስ ከተጀመረ በኋላ ነበር/ነው ። ያውም ብሄራዊ ወይም የአገራቸውን ዋና ከተማቸውን ፈርሶባቸው ሳይሆን –ታክስ ተጨመረብን፣ ኑሮ ተወደደብን፣ሕገመንግሥታችን ለመቀየር ታስቧል ወዘተርፈ  በሚል ነበር ። ይህንን የኢትዮጵያውያን ሁኔታ በሚከታተል የዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ/ግሎባል ኮምኒቲ ዘንድ ኢትዮጵያውያን እንደ ሰው ሳንሆን  እንደ አህያና እንደ ከብት ሳንታይ አይቀርም ብዬ እገምታለሁ ።

ለ) ከደርግ ቀይ ሽብር ጀምሮ ያለው  ትውልድ  ፈሪ እንዲሆን ካደረጉ እውነትነት  ካላቸውና ግምታዊ ምክንያቶች ጥቂቶቹ  ፡-

- በቀይሽብር ወቅት ታሥረው ፣ ሰቆቃ  ተፈጽሞባቸው ፣ ኢቻ ጓዶቻቸው ካጠገባቸው ተወስደው  በዛው ሲቀሩ ያዩ ፣ ዕድለኛ ሁነው  ከስር ሲወጡ –የሚወዳቸው ጓዶቻቸውን ፣ ወንድሞቻቸውን፣ እህቶቻቸ ውን ፣ ቤተዘመዶቻቸውና ሠፈርተኞቻቸውን ወዘተርፈ – መገደል/መረሸን ወይም መጥፋት የሰሙ ወጣቶች  እነዚያ ኩነቶች ስለአስደነገጣቸው ፣ ቅስማቸውና ሰነልቦናቸውን ሰለተሰበረ ፣በድኽረ ፍርሃትና  በመንፈስ ጭንቀት ምክንያት ከትግል ራቁ ።
- በደርግ ቀይሽብር ወቅት የአቅመ ትግል ደርሰው –ትግል ውስጥ ያልገባውና ብላቴና ወጣት የነበሩ – ታላቅ ወንድሞቻቸውን፣ እህቶቻቸውን፣ የአክስቶቻቸውን፣ የአጎቶቻቸውን፣ የጎረቤቶቻቸውን፣የሠፈሮቻቸውን ወጣቶችን አስከሬን– በቤታቸው ደጃፍ፣ በጎረቤቶቻቸው ደጃፍ፣ በየመንገድ ዳር፣ በየጉራንጉሩ ወዘተርፈ  ተጥሎ ያዩ ፣የተመለከቱ፣ በዛ ውስጥ ያለፉ ፣ እነዛ ኩነቶች ቅስማቸውን /ሞራላቸውን ሰለበረው ፣ በስነልቦና  ስብራትና  ፍርሃት  ከዛ በኋላ የመጡ – ጸረ አገራዊና ሕዝባዊ አንድነት ፣ ኢትዮጵያ ጠል፣አክራሪ ብሄርተኛ  ገዢዮችና ሥርዓቶቻቸውን እንዳይታገሉ ተጽኖ አደረገባቸው ፤ገታቸው  ።  የስነ ዕድገት፣የስነአእምሮ እና የስነልቦና ተመራማርዮች እየተደበደበ ፣እየተዋከበ ፣እየተጨነቀ ፣እየተሸበረ  የሚያድግ ህጻን/ልጅ  ዕድሜ ዘመኑ ሙሉ  ፈሪ ፣ ታዛዥ፣ ተምበርካኪ ወዘተርፈ ሰው ይሆናል  ይላሉ ።

- በደርግ ቀይሽብር ግዜ ህጻን የነበረና ከዛ ወዲህ የተወለደ ትውልድ ፦እኛና እነሱ በተባለ፣ በብሄር ብሄረሰብ ኢፓርታይድ በተከፋፈለ፣ የብሄር ብሄረሰብህ አባል ካልሆኑ ጋር አብረህ አትብላ ፣አጠጣ፣አትገናኝ፣ ያንተ ዘውግ ወይም ጎሳህ ያልሆኑ ሁሉ ጠላትህ ነው/ናቸው በሚል በተዋቀረ–structured የፖለቲካና የማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ ያደገ በመሆኑ ፤ በኢትዮ_ብሄር ብሄረሰብ  ወይም በዜግነት ኢትዮጵያዊነት ስነልቦና፣ንቃተ ኅሊናና አስተሳሰብ አውድ ባለማደጉ
- ግለኝነትና ለኔ ብቻ ባይ ማኅበራዊ ባህልና ማኅበረሰብ ባሰፈነ የአገዛዝ  ሥርዓቶች ውስጥ ተወልዶ ማደግ ። ሃብትና ንብረት ለመውረስ  ወላጆቹን የሚገል ፣ (ሚስት ባልዋን አሳፍና ድብቃ ሙቶ ተቀበረ ብላ የማስመሰል ሃዘን የምትቀመጥበት ፣ባል ሚስቱን አሳፍኖ ደብቆ ሙቷ ተቀበረች ብሎ የማስመሰል ሃዘን የሚቀመጥበት  ፣ ውርስ ላለማካፈል ወንድሙን ወይም እህቱን ፣የሚሰውር ፣ ጫካ ወስዶ ከዛፍ ግንድ አስሮ ለአውሬ የሚሰጥ/የምትሰጥ፣ በቦጎ አድርጊዮች ገንዘብ ለመክበር –ልጇን በመድሃኒት የምታሳብድ፣ በሽተኛ የምታደርግ ፣ የሚያሳድጋት እህቱን በመድሃኒት የሚያሳብድ፣በሽተኛ የሚያደርግ ፣የሚያሳድገው ወንድሙን በመድሃኒት  የሚያሳብድ/የሚያስገድል፣ከሬሳ ጋር የሚተኛ፣ፍትሆተ ሥጋ የሚፈጽም፣ አስከሬን ከሆስፒታል ሰርቆ የሚሸጥ ፣ በአክስትና በአጎት ልጆጅ መካከል ጋብቻ የሃረርጌ ቆቱዎች፣ የአደሬዎችና የአረቦች ባህል ቢሆንም  ፤ ቀደም የዚህን ዓይነት ባህል ባልነበረበት ማህበረሰብ ወስጥ  አብሮ በአንድ ቤት ባደጉ በአክስትና በአጎት ልጆች መካከል ጋብቻ በሚፈጽምበት ወዘተርፈ ፤  ኢሰዋዊ ባህሪና  ፍጹም  ግለኝነት  ማኅበራዊ ባህል በፈጠረ/ባሰፈነ  የአገዛዝ ሥርዓት/ሥርዓቶች ውስጥ ተወልዶ ያደገ ትውልድ በመሆኑ
- የትውልዱን ንቃተ ኅሊና የሚያንጹና የሚያታግሉ –የህብዕም ሆነ የይፋ የፖለቲካ፣ የሞያ፣ የማኅበራዊ፣ የተማሪዮች ወዘተርፈ ድርጅቶች አለመኖር፤ ከዚህ ጋር በተዛመደ ከወያኔ ሥርወ አገዛዝ  ጀምሮ የድኅረ ዘመናዊ ማኅበራዊ ሚዲያዎች ሚና –post modern social media እንደ አሸን ፍልቷል ። አብዛኞቹ የዩቲዩብ ማኅበራዊ ሚዲያዎች መነሻ ዓላማ የነዋይ ገቢ ምንጭ ማሳደጃ ናቸው ። ማኅበረሰቡን ለማንቃት–በማኅበራዊ አንቂነት መርህ የተመሠረቱ

ቢኖሩም የኢሊቶች ፖለቲካዊ ታይታ መተንፈሻና መለዋወጫ ከመሆን ያለፉ አይደሉም ። ማለት አውደ ሕዝቡን አንቅተው፣ አደራጅተው፣ ስልትና እስትራተጂ ነድፈው የሚታግሉ አይደሉም ።

- የትውልዱን–አእምሮ፣ ቅስም/ሞራል ፣ ስነልቦናና አስተሳሰብ በሚሰልቡ እና የአካል ጥንካሬ በሚያሳጡ/ደካማ በሚያደርጉ ፤ እንደ ማራዋናና ጫት ባሉ ዕጾች፣ አልኮሆል እና ካደጉ ባዕድ አገራት በሚመጡ ጎጂ ፖፕ ካልቸር እንዲጠመድ በመደረጉ ፤ ሥርዓታዊ/systemic በመሆኑ
- በዘመናዊ ትምህርት አማካኝነት የሚገኙ ጥሩ ዕውቀትን፣እውነትን፣ ስነጽሁፍን፣ ስነኪነት/አርትስን ወዘተርፈ ቦታ ባልሰጡ ገዢዎችና የአገዛዝ ሥርዓቶቻቸው ውስጥ ተውልዶ በማደጉ
- ሥርዓተ ትምህርቱ ፦ ብዛት/መጠን እንጂ ዓይነት/ጥራት የሌለው ፣ ዩኒቨርስቲ ደርሶ በቅጡ (እንግሊዝኛ ጽሁፍ ማንበብ፣ መጻፍና በእንግሊዥኛ መግባባት) የማይችል ዜጋ የፈጠረ፣ (ታዛዥነት፣ አደግዳጊነት፣ ተለማማጭነት ወዘተርፈ) እንጂ ለምን? ስለምን? እንዴት? ወዘተርፈ በሎ የማይጠይቅ ዜጋ የፈጠረ ፣የትውልዱን –ጭንቅላት፣አስተሳሰብ እና አድማስ ያቀጨጨና ያጠበበ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በማለፉ ወዘተርፈ ፤ እነዚህንና ሌሎች እዚህ ጋ ያልተጠቀሱ ሁኔታዎችና የነዚህን ተጽኖች ትውልዱን ፈሪ አደረገው ። እንደ አህያ የሚጫን፣ እንደ ከብት የሚነዳ፣ እንደ በቅሎና ፈረስ የሚጋለብበት፣ ቋንቋው እንደ ተቆረጠ ባሪያ ሆነ ። ድፍረት፣ወኔና አንድነት እንዳይኖረው አደረገው።

……"One man is an oppressor because many are slaves.Let us despise the slaves"..–ብዙዎቹ ባሪያ ስለሆኑ አንድ ሰው ጨቋኝ ሆነ ወይም የአንድ ሰው ጨቋኝ መሆን የብዙዎች ባሪ መሆን ነው ወይም የአንድ ሰው ጨቋኝ መሆን የብዙዎች እንደ ባሪያ መገዛት ነው ፤ ስለሆነም ጨቋኙ ሳይሆን ባሪያዎች መናቅ ፣መተቸት፣ ማውገዝ ወዘተርፈ አለብን ማለቱ ይመስላል (James Allen As a Man Thinketh,2019, p62).

"The truth is that oppressor and slave are cooperators in ignorance and, while seeming to afflict each other are in reality afflicting themselves –ጨቋኝና ባሪያ

*ወይም የባሪያ ጌታና ባሪያ ህብረት ፈጥረው ፣በህብረት እንዲኖሩ ያደረጋቸው እውነታ/ምክንያት ድንቁርና ነው ። የተጎዳዱ ማለት ጨቋኙን ባሪያውን የጎዳ፣ ባሪያው ጌታውን የጎዳ  ይምሰላቸው እንጂ ሃቁ ግን ሁለቱም ራሳቸውን እየጎዱ ነው ። ጨቋኙ የባሪያ ጌታ በድንቁርናው ምክንያት ሰው ስለሚጮቁን ራሱን እየጎዳ ነው ። ተጨቋኙ ማለት ባሪያው በድንቁርና ምክንያት ራሱን ነጻ ስለአላውጣ ራሱን እየጎዳ  ይኖራል ” ማለቱ ይመስላል (ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 64)።  እነዚህ የጄምስ አለን ምሳሌዎች የወቅቱን የአገራችን ሁኔታ የሚያንጸባሩቁ ይመስለኛል። በገዢዮች፣ በአገዛዛቸውና በአውደ ሕዝቡ መካከል ያለው ግንኙነት/ሪሌሽን ምን እንደሚመስል ማሳያዎች ናቸው ።*

***ማስታወሻ/መልዕክት፡-*** *የአገራችንን ሥርዓት ትምህርት ወይም የትምህርት ሥርዓት መበላሸት በአሁኑና በመጻኢ ትውልድ እንዲሁም በብሄራዊ ዕድገት ላይ የሚኖሮ አሉታዊ ተጽኖ አሳስቧቸው እንደተነሱ ኢትዮ–ምሁራን ፤ከደርግ ቀይሽብር ግዜ ጀምሮ እስካሁን ያለው ትውልድን–'ስነልቦና፣ስነአእምሮና  ማኀበራዊ ባሕል (psychodynamics, mental health and social culture) እንዲሁም ከወያኔ በትረ አገዛዝ ጀምሮ ያለውን የአማርኛን አጠቃቀም ይዘትና ጉራማይሌነት/ መዛባትን የሚያጠኑና መፍትሄ የሚጦቁሙ እየዘርፉ ሊሂቃን ያስፈልጋሉ ባይነኝ ። ምንጩ ባላገኘውም –በኢትዮጵያ ከአምስት ኢትዮጵያውያን አንዱ/አንዷ የአእምሮ ህመምተኛ ነው ወይም ናት ተብሎዋል የሚል ሰምቼአለሁ ።*